# ኮቪድ-19 አደጋን ለመታደግ የኔቫዳ የጤና እቅድ

" ዋነኛው አካሄድ ሁሉም ኔቫዳውያን እቤታቸው መቆየትና ለሕይወት አስፈላጊ ያልሆኑ መስሪያ ቤቶችና ቢዝነሶች በጊዚያዊነት ለ 30 ቀናት ለተገልጋዮች ቢሯቸውን ቢዘጉ ነው፡"

ገቨርነር ስቲቭ ሲሶላክ፣ ማርች 17, 2020

*ይህ ኔቫዳ የኮቪድ.19 አደጋን ለመታደግ የወጣ እቅድ የወጣው የገቨርነር ሲሶላክ፣ ማክሰኞ ማርች 17፣ 2020 የሰጠውን ጋዜጣዊ መግለጫ መመሪያ በመከተልና ገቨርነር ሲሶላክ ማርች 12፣ 2020 የኔቫዳ ሕገ መንግሥት አንቀጸ 5፣ ቁጥር 1 በሚያዘው "የስቴቱ የበላይ ሥልጣን የኔቫዳ ገቨርነር በሆነው ዋና አስተዳዳሪ ይሆናል የሚለውን ተከትሎ" በሰጠው ጊዚያዊ አዋጅ ተንተርሶ ነው።*

የዚህ እቅድ ግብ ሰዎች አስፈላጊ ባልሆነ ጉዳይ እንዳይሰባሰቡና በቫይረሱ የተለከፉ ሰዎች ቫይረሱን ለሌሎች በቀላሉ እንዳያስተላልፉ በማድረግ የኔቫዲውያንን ጤናና ሰላም ለመጠበቅ ነው። ራሳችሁን "ሰዎች ረዘም ላለ ጊዜ በ 6 ጫማ ርቀት ላይ የሚሰባሰቡት የት ነው? ብላችሁ ጠይቁ-- እንደዚህ ካለ ቦታም አትድረሱ።

የኮቪድ _19 ችግር ለመቅረፍ እንደሚወጡ እቅዶች ሁሉ፣ ገቨርነሩ፣ የኔቫዳ የጤና ጉዳይ ማእከልና ያካባቢና የስቴት ባለስልጣናት ጉዳዩን ከሕዝቡ ጤና ፍላጎት አንጻር በቅርብ በመከታተል መለወጥ የሚገባውን ይመለከታሉ።

ይህን እቅድ በቶሎ በመተግበር፣ በሰዎች መሃል ያለውን በአካል የመቀራረብ ሁኔታ በማስቀረትና የቅርብ ግኑኙነትን በማስወገድ፣ መሰባሰብን በመገደብ ከዚህ በፊት የተከሰቱ ወረርሽዎችን በመቅጨት ከሞትና በሽታ ለመታደግ ተችሏል። የበሽታውን በኔቫዳ ከመስፋፋት በመገደብ፡

- ተግቢ ክትባትና ፍቱን መድሃኒት እስኪገኝ ድረስ በኮቪድ _19 የሚለከፉ ኔቫዳውያንን ቁጥር መቀነስ።
- በበሽታው በጣም ሊጠቁ የሚችሉ የእድሜ ባለጸጋ ኔቫዳውያንንና፣ ቁዋሚ የሆነ በሽታ ያላቸውን ሰዎች አስፈላጊ መከላከል ማድረግ።
- የሕክምና ተቋሞቻችንና ሃኪሞቻችንን በሚገባ በመጠበቅ፣ ከኮቪድ-19 ብቻ ሳይሆን በሌላ በሽታዎች ለተጠቁ ሰዎች አገልግሎት እንዲያበረክቱ ማድረግ።
- ከረዥም ጊዜ አንጻር በኮቪድ-19 ሳቢያ የሚመጡትን ጉዳቶች ማሳነስ።

# መቀራረብን ለማስወገድ የሚጠቅሙ ሃሳቦች

ከቤተሰብ ውጭ ኔቫዳውያን ከ 6 ጫማ ያላነሰ መቀራረብ ማስወገድን ማዘውተር መልመድ።

ማስወገድ የሚያስፈልጉ ልምዶች፡

- በርከት ብሎ መሰብሰብ
- ልጆች ከጓደኞቻቸው ጋር ለማደር አለመሄድ
- ወደ ሙዚቃና ትያትር ትእይንቶች አለመሄድ
- ለጫወታ መቀጣጠር
- የስፖርት ትእይንቶች
- እንግዳ ማስተናገድ
- በቤታችሁ የግድ የማያስፈልጉ ሰራተኞች
- ወደ ሞሎች አለመሄድ
- ወደ ጂም ቦታዎች አለመሄድ

## መሰብሰብን በሚመለከት የዕቅዱ ገደቦች

ስብሰባዎችን ማስተላለፍ ወይም መሰረዝ

ይህን ዕቀድ በሚመለከት፣ "መሰብሰብ" ማለት ወጭ ይሁን እቤት ውስጥ ባንድ የስብሰባ ቦታ ሰዎችን ማምጣት ማለት ነው።

መሰብሰብ ሲባል፣ አደጋው የሚለካው በግለሰቦች መሃል ባለው መቀራረብ እንጂ በሚያከናንውኑት ጉዳይ አይደለም። አደጋው የሚለካው በስብስቡ አነስተኛ መሆን ሳይሆን በሰዎቹ መሃል ባለው መራራቅ እንጂ።

- በሰርጋችሁ ደስተኞች እንድትሆኑ እንፈልጋለን፤ ጊዜው ዘመድ አዝማዱን መሰብሰብ መሆን የለበትም -- በተለይ መሰባሰቡ መጓዝን የሚጨምር ከሆነ። ድግሱን አደጋው በሚቀንስበት ጊዜ ማድረጉ ይመረጣል።
- ቤተ ዘመድ መሃል ሞት ቢከሰት፣ ሽኙቱን በቀባሪዎች ብቻ አድርጉ። የቀብር ስርአቱ በቤት ውስጥ ከማድረግ ወጭ አድርጉት።
- ገቨርነሩ ቤተ እምነቶች ይዘጉ ማለት አይችልም አይፈልግምም። ሆኖም ግን ተከታዮቻችሁን ባንድ ላይ ሳተሰበስቡ የምታስተምሩበትን መንገድ እንድትሹ ለሃይማኖት መሪዎች ያሳስባል።

## የግድ አስፈላጊና አላስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችና ክፍሎች

**የግድ አስፈላጊና አላስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችና ክፍሎች የሚከተሉት ሲሆኑ ዝርዝሩ ግን ሁሉንም አይጠቀልልም፡**

- የእሳት አደጋ፣ ሕግ አስከባሪ ድርጅቶች፣ አስቸኳይ የሕክምና አገልግሎቶችና የአደጋ መከላከያ ድርጅቶች
- የሕክምና ድርጅቶች
- በምግብ አቅርቦት፣ መጠለያ፣ ለተጎጂ ሰዎች አስፈላጊ የሆኑ የሕብረተሰብ መገልገያዎች
- በኔቫዳ ሕግ ምዕራፍ 704 አገልግሎት (utitlities) ተብለው የተዘረዘሩ ድርጅቶች
- ቆሻሻ ሰብሳቢ
- የቤት ጥገና አገልግሎቶች
- የመኪና ጥገናና የጭነት አገልግሎት ማእከሎች
- ግሮሰሪ፣ ሱፐርማርኬት፣ የቤት መጠገኛ (ሃርድዌር) ሱቆች፣ ትንንሽ (ኮንቪኔንቸ ስቶረስ) ሱቆች
- ፋርማሲዎች፣ የህክምናና ባዮኬሚካል ተቋሞች
- ፖስታ ቤትና፣ እቃ ላኪ ድርጅቶች
- ቤንዚን ቤቶችና የጭነት መኪና ማቆሚያዎች
- ባንኮችና የገንዘብ አገልግለቶች
- የእንስሳ ሃኪም ቤቶችና የእንስሳ ቁሳቁስ መሸጫዎች
- ልብስ ማጠቢያ ቤቶች
- ምግብ ማዘጋጃ ተቋማት
- እርሻ፣ እንስሳ ማርቢያና ማሳደጊያ
- ማከፋፈያ፣ እቃ ማከማቻ፣ ማከፋፈያና ስፊ የማከፋፈያ ድርጅቶች
- የሕዝብ ማመላለሻ
- አስፈላጊ ሆቴሎች፣ የንግድ ህንጻዎች፣ ዶርሚቶሪ፣ መጠለያና የመንገድ አዳሪ መጠጊያ
- በፍቃድ ሰጪ ድርጅቶችና በኮቪድ_19 መምሪያ የተፈቀደላቸውመዋእለ ሕጻናትና የልጆች መዋያ

እነህ መስሪያ ቤቶች እንዲከፍቱ ቢፈቀድላቸውም፣ የኔቫዳ የጤና ጉዳይ ማእከል ሰራተኞቹና ተገልጋዮቹ አስፈላጊው የርቀት መጠንን እንዲጠብቁ በጥብቅ ያሳሳባል። በተጨማሪም፣ ድርጅቶቹ፣

- ሰራተኞቻቸው አስፈላጊውን የሃይጅን ልምድ፣ እጆቻቸውን ቶሎ ቶሎ በውሃና ሳሙና ቢያንስ በየ 20 ደቂቃ ውስጥ እንዲታጠቡ ያሳስባል
- የበሽታ መከላከያ ማእከል (CDC) አካባቢን ማጽዳትና ህዋሶች ማጥፋት በሚመለከት፤ምግብ በሚቀባበሉበት/ በሚያነሱበት ወቅት የሚጠቀሙባቸውን ጠረጴዛዎችና የምግብ ማዘጋጃ ጠረጴዛዎች የሚጸዱበትን ጊዜ በማእከሉ ከተሰጠው ጊዜ በተጨማሪ ማጽዳት ያስፈልጋል።

ሌሎች የስራ ቦታዎች፣ የሕግ አገልግሎቶች፣ የሥራና ያስተዳደር አማካሪዎች፣ ፕሮፈሽናላ ኢንሹራንስ አገልግሎቶች ስራተኞቻቸው ከቤታቸው፣ ቴሌኮምዩት እንዲያሰሩ ያበረታታል።

ይህን ማድረግ ካልቻሉ፣ በኔቫዳ የጤና ጉዳይ ማእከልና በሲዲሲ በወታው መመሪያ መሰረት አስፈላጊውን የርቀት መጠን እንዲጠብቁ ያሳስባል።

## የግድ አስፈላጊ ያልሆኑ አገልግሎቶችና ክፍሎች፣ በነዚህ ብቻ ግን አይወሰኑም፡

- የመዝናኛና የመድሰቻ፣ ማለት ስትሪፕ ክለብ፣ ሴተኛ አዳሪ ቤቶች፣ ካዚኖዎች፣ የሙዚቃ ቤቶች፣ ትልልቅ አዳራሾችና ካፌተሪያ
- የመዝናኛና የስፖርት ቦታዎች፣ የህብረተሰብ መዝናኛ ቦታዎች፣ የጤና ክለብ፣ ጂም፣ ዮጋ
- የውበትና የግል መቆናጃ አገልግሎትና ቦታዎች፣ ጸጉር ቤት፣ የቅባት መቀባቢያ ቤቶች፣ የጥፍር ቤቶችና ስፓዎች

- የችርቻሮ ቤቶች፣ ፋርማሲና ሌላ የጤና አገልግሎት የሌላቸው የንግድ ሞሎች። ቸርቻሪዎች ስራቸውን በማድረስና በማንሳት ብቻ እንዲያደርጉ ይመከራሉ።

## የምግብና የመጠጥ አገልግሎት ሰጪዎች መመሪያ

ምግብ ቤቶችና ቡና ቤቶች የኮቪድ _19 መስተላለፍ ለማስቆም በገቨርነሩ ታዘዋል። ሆኖም ግን አገልግሎታቸውን ተገልጋዩ በማንሳት፣ ወደ ቤት በማድረስና በመኪና በማንሳት ስራቸውን ማካሄድ ይችላሉ። በምግብና ቡና ቤት ውስጥ መብላት መጠጣት ግን ተከልክሏል። እኒህ አይነት ድርጅቶች ግን ተገቢውን የመራራቅ መመሪያ መከተል ይኖርባቸዋል። ተጨማሪ ማሳሰቢያ፡

- የእርዳታ ምግብ ማከፋፈያ ቦታዎች፣ በት/ቤት መዘጋት ሳቢያ ለተማሪዎች ምግብ የሚያቀርቡ፣ ግሮሰሪዎች ክፍት ሁነው አገልግሎታቸውን ይቀጥላሉ።
- ለህክምና አገልግሎት ሰጪዎችና ሌሎች አስፈላጊ ቦታዎች ክፍት ይሆናሉ።
- የእርዳታ ቡፌና የምግብ ጣቢያዎች አቅራቦታቸውን በባኮ ያድርጉ ወይም የእጅ ጓንቲ ባደረጉ ሰራተኛና በነ አድራጊዎች ይካሄዳሉ።
- በኔቫዳ የሚሰሩ ምግብ ቤቶች፣ ቡና ቤቶች፣ ፓቦችና የወይን ቦታዎች አግልግሎታቸው በመኪና ለሚያነሱ፣ ወደ ቢታቸው ለሚወስዱና በቤት የማድረስ አገልግሎት ብቻ ይሆናል። በሌላ መመሪያ እስኪቀየር ድረስ በአገልግሎት ቤቱ ውስጥ መብላት የተከለከለ ነው። ይህ መመሪያ ምግብ ለመብላት ሰው በሚሰበሰብባቸው ቦታዎች እንደ ፉድ ኮርት፣ ቡና ቤቶች፣ በምግብ አቅራቢዎች በተዘጋጀ ቦታ፣ ክለቦች፣ ቦውሊንግ መጫወቻ ሁሉ ይተፈጻሚነት ይኖረዋል።
- ፓቦች፣ ወይን ቤቶችና ቢራ በቶች የተሟላ የምግብ አቅርቦት ማዘጋጃ ኩሽና የሌላቸው ዝግ ይሆናሉ።

እንዲከፈቱ የተፈቀደላቸው የምግብ አገልግሎት ሰጪዎች፡

- በርካታ ተጠቃሚነት ያላቸው፣ እንደ ሽንት ቤት አይነቶችን፣ ቀደም ሲል ሲደረግ ከነበረው ተጨማሪ ማጽዳት ማድረግ ይኖርባቸዋል።
- ለሰራተኞች ደግም ጥብቅ የሆነ የሃይጅን መመሪያ ቶሎ ቶሎ እጃቸውን በውሃና ሳሙና ከ 20 ደቂቃ ያላነሰ መታጠብ እንዲለባቸው ማድረግ።

## ቁማር (ጌሚንግ)

የቁማር መጫወቻ ማሽኖች፣ ጠረጴዛዎችና ሌሎች ከቁማር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ሁሉ እንዲዘጉ ገቨርነሩ አዟል። በቁማር ቤት የሚገኙ ምግብ ቤቶችና ባሮች ለሌላ ምግብ ቤቶችና ባሮች የወጣው መመሪያ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## ካናቢስ (ማሪዋና)

ለካናቢስና ህክምና በሚመለከት የንግድ ፍቃድ ያላቸው ድርጅቶች ሊከፈቱ የሚችሉት በሰራተኞቻቸው እንዲሁም በደንበኞቻቸው መሃል የሚገባውን የርቀት ደንብ ማስከበር ከቻሉ ብቻ ነው። የኔቫዳ የጤና ጉዳይ ማእከል ተጠቃሚዎች ወደ ሱቁ በመሄድ ምትክ **በቤት አድርሾች እንዲጠቀሙ** አበክሮ ያሳውቃል።